Remove Watermark Now

# ሰመመን



pdfelement

ከሲሳይ ንጉሡ

Remove Watermark Now
pdfelement
Zion
Book
t.me/Zionbook

# ሰመመን

ሲሳይ ንጉሡ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
1978
አዲስ አበባ

# ሰመመን

ከሲሳይ ንጉሡ

ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት
1978
አዲስ አበባ

Remove Watermark Now
pdfelement

# ምዕራፍ ሦስት

አቤል ከፍልስፍና መምህሩ የተቀበለውን የ[illegible] ጽሑፍ ሲሸሸው ሰንብቶ፣ በአራተኛው ቀን የገጹን እንዳለው ። አልጋው ላይ ጋደም እንዳለ ነበር — ለማንበብ የፈለገው ። ከሰ የሚጠጣ ይመስል ፊቱን አጨማዶ ገለጠው፤ የመጀመሪያውን ገጽ ሳያነብ እያገላበጠ ከመሐል ደረሰ ። እንደ ገና ወደ ኋላ ተመለሰ ። የራሱ የእጅ ጽሕፈት አስጠላው ።

'እሜ !' አለ፣ በመሰላቸት ድምፅ ። 'አሁን ምንን ነው የማሻሽለው ? የቻልኩትን ያህል ሠርቻለሁ፣ በቃ !'

ገና ሳያነበው፣ የሚሻሻል ነገር የለበትም ብሎ ወሰነ ። እጆቹ ሳይታዘዙ የጥናት ጽሑፉን ወረቀት ከደኑት ።

'ምን ይመጣብኛል ?' ሲል አሰበ። እንደ ገና ባለሥራው ተሰቀል የሚለኝ የለ ። ያው ወድቆ መብረር ነው ። ይህ ደግሞ በእኔ አልተጀመረ ። ለምን ራሴን አስጨንቀዋለሁ ?'

የናታን በድንገት በሐሳቡ መምጣታቸው ድንገት አስበት ። ወረቀቱን ተቀብለውት ሲወጣ የተናገሩት ቃላት ታወሰው ።

“ሐሳብ ውስጥ ገብተህ ወይም ተቻኩለህ ይሆናል እንጂ፣ አንተ እንዲህ ወይነት ሥራ እንደማትሠራ እተማመናለሁ ።”

“ዕዳ እኮ ነው” አለ በሐሳቡ ። 'እሳቸው ደግሞ ለምን የሰው ችግር አይገባቸውም ? ፍቅር ወጥመድ ውስጥ ለገባ ተማሪ ጥናትና ሥራ ምንኛ እንደሚያስጠላት ለምን አይረዱልኝም ? . . . ያውም አቅፎ ወይም ስሞ ወይም ተዳርሶ ማስከን በማይቻል በወይን ፍቅር ለተለከፈ ተማሪ ! ነገር የጠፋው ቀድሞ ነው ። ትምህርት አስተቀምጦ ፍቅር የተጀመረ ዕለት !'

ማፍቀር በአንድ አጋጣሚ የሚከሠት የሕያውነት ነጸብራቅ ሳይሆን ራሱ ሥራዬ ብሎ ትትቶ ያመጣው ይመስል፣ ገና የመጀመሪያ ዕለት ትዕግሥት ላይ ያረፉት ወይናቹን በልቡ

# ምዕራፍ አምስት

ከምሽቱ ሦስት ሰዓት አካባቢ ይሆናል ። ማርታ ገና ከውጭ አልገባችም ። ትዕግሥትና ሁለት የመኝታ ክፍል ጓደኞች አልጋቸው ላይ ጋደም ብለው ፤ ከመጀመሪያ ዓመት ኮርስ አንዱ የሆነውን የኢትዮጵያ ታሪክ እያነበቡ ይጠያየቃሉ ።

የመኝታ ክፍላቸው በር ሳይንኳኳ ተከፈተ ። ቤተልሔም አሰግድ አንገቷን ብቻ ወደ ውስጥ ብቅ አድርጋ ተመለከተቻቸው ።

"እ ቤተልሔም ፣ ግቢ" አሏት ሦስቱም በአንድ ድምፅ ።
" ማርታ አልመጣችም እንዴ ? " ስትል ጠየቀች ።

" ገና ፣ ትመጣለች " አሏት ሁሉም ። ወደ ውስጥ ገብታ ትዕግሥት አልጋ ላይ ከጎኗ [illegible] ተቀመጠች ።

" ምነው ዘገየች ፣ የት [illegible] ነበር ? " ከሰች በኋላ ፣ ቤተልሔም [illegible] ጠየቀችና ፣ "እንጃ ፣ ምሽት ሰዓት ከሆነ በኋላ " ኧ ! ለመሆኑ ብትመጣስ ዘበኞቹ ያስገቧታል ብለሽ ነው ?" አለች ፣ ተስፋ በቆረጠ አነጋገር ።

" ከመጣችስ ያስገቧታል ፣ ልጅትየ ማርታ ናት " አለች ትዕግሥት ፣ በቀልድ ዐይነት -የማርታን ትልቅነትና ለመግለጽ ። በርግጥም ማርታ አምሽታ በመጣች ቁጥር " ጥብቅ ነን "የሚሉትን የጥበቃ ጓዶች ጥርሷን እያሳየች ውሃ አድርጋቸው ነው የምትገባው ።

" ይልቅ " አለች ትዕግሥት በመቀጠል ፣" ይልቅስ መምጣቷን ተጠራጠርኩኝ " ለቤተ ልሔምም ጉዳዩ እንግዳ ነገር አይደለም ። ይልቁንም በተለያዩ ጊዜ አብረው ነው ምሽቱን የሚወጡት ። ቤተ ልሔምን ከትዕግሥት ያስተዋወቀቻት ማርታ ናት ። የእነሱ ጓደኝነት ግን ከውጭ ጀምሮ ነው ከዘለቀ ዓመት ያህል አሳቸው ። እንዲያውም ቤተ ልሔም

# ምዕራፍ ዘጠኝ

አንድ የተፈጥሮ ሳይንስ ምሩቅ መምህር ለድኅረ-ምረቃ የሚያበቃቸውን የጥናት ጽሑፍ መዘክር ከማቅረቡ በፊት አማካሪው ዶክተር አጥናፉ የሰንደል ተክሉን እንዲጎበኙለት ጋበዛቸው ። ፕሮጀክቱን የሚሠራው በሰንደል ተክል ነበር - የተለያየ አፈር በሰንደል አበቃቀል ላይ የሚኖረውን ተጽዕኖ አጥንቶ ለማቅረብ ።

የናታን ጉዳይ ባይመለከታቸው ፕሮጀክቱን አቅራቢው መምህር በግል ወዳጅነቱ እንዲያዩለት ስለ ጋበዛቸው ከዶክተር አጥናፉ ጋር ሔደው ነበር ። ለጥናት ተክሎች ከተሠራቸው ጎጆ ውስጥ እንደገቡ በጣሳ ጉች ጉች ብለው የተተከሉትን የሰንደል ተክሎች አትኩረው መጐብኘት ጀመሩ ። ከመስታወት ቤቷ ላይ አረንጓዴው ቀለም ሙልጭ ብሎ በለጠፋ ታጠሉው ሌላ ከተማ የገቡ ይመስል ነበር ።

" ለምን የሊሆች ጎጆ ስም ተቀይሮ ' ኋይት ሀውስ ' አይባልም ! " አሉ የናታን በቀልድ ዐይነት - ነገር ግን ወቀሳን ባዘለ አነጋገር ። አረንጓዴው ቀለም ከጠፋ በኋላ ፣ " ግሪን ሀውስ " ማለቱ ትርጉመ-ቢስ መሆኑን ለመጠቆም ነበር ። ' ኋይት ሀውስ' እንዳይባልማ የተክሏን ጎጆ ከአሜሪካን ቤተ መንግሥት ጎን ማስቀመጥ ይሆናል ! " አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ ቀልድን በቀልድ በመመለስ ።

ምንም አስተያየት ሳይሰጡ ስምንት የተክል ቆርቆሮዎች ማለፋቸው አስጎብኚውን ሳያበሽቀው አልቀረም ። ከኋላ ከኋላቸው እየተከተለ ፣ " ግሩም ነው ! " የሚል ድምፅ ይጠብቅ ነበር ።

" ይህ የየት አገር ዐፈር ነው ? " አሉ ዶክተር አጥናፉ ፣ ዐፈሩ በደንብ ተስማምቶአቸው ከሁሉም ፋፍተው የበቀሉትን ዐምስት ያህል የቆርቆሮ ተክሎች እየተመለከቱ ።



Remove Watermark Now

# ምዕራፍ ዐሥር

" ራስ ግሪል " የምትል ዓርማ ከደረቱ ላይ የለጠፈ አስተናጋጅ ፤ " ምን ልታዘዝ ? " ሲል ከፊቱ መጥቶ ቆመ ።

" እስቲ ቀዝቃዛ ቢራ " አለ ለማ በዓይኑ እየተመለከተ ።

ዘጠኝ ከዐሥር ሆኖ ነበር ። ' በታው ጠፍቷት ይሆን እንዴ ? ' ሲልአሰበ ፤ ምናልባት ዋናው ራስ ሆቴል ሔዳ እንደሆን በሚል ግምት ። ነገር ግን ቀጠሮአቸውን በደንብ ያስታውሳል ። "ራስ ግሪል ፤ ቅዳሜ በዘጠኝ ሰዓት" ሲላት ፤ ጥቂትም ግር ሳይላት ነበር ፤ ቀጠሮውን የተቀበለችው ።

' እንዴት አባቷ ቀጠሮው በታ ቀድማ አትገኝም ?' የሚል ትምክህት ተሰማው ። ለጊዜው ተፈላጊ በመሆን ዐሥር ደቂቃ አሳልፎ የመጣው ቀድማ ትጠብቀኛለች በሚል ግምት ነበር ።

አሳላፊው ቢራውን ይዞለት መጣ ።

ለማ የቢራውን ቅዝቃዜ ለመገመት ጠርሙሱን በእጁ ጠበቅ አርጎ ከጨበጠ በኋላ አስከፈተ ። ሁለቴ ተጎንጭቶ ግማሽ ወገቡ ላይ አደረሰው ። የዕለቱ ወበቅ ሌላ ጉዳይ ነበር ። ኮቱን አወለቀ ። ከፊት ለፊቱ በከረባት ታንቀው የተቀመጡትን ወፍራም ሰውዬ ተመልክቶ ፤ ሙቀት በመቋቋም ችሎታቸው ተደነቀ ።

ደቂቃዎቹ ወደፊት ተራመዱ ። ወፈር ያለች አጭር ልጅ ግን ብቅም አላለች ። አምስት ደቂቃ ሳይሆን ሙሉ ቀን የጠበቃትን ያህል ስሜቱ ተቁነጠነጠ ። ከአሁን በፊት ሁለት ጊዜ ሴቶች በቀጠሮ ቀጥተውታል ። ብዙ ሴቶች በመጀመሪያ ቀጠሮ ላይ እንዲህ እንደሚያደርጉ ያውቃል ። ርካሽ እንዳይመስሉ የሚያደርጉት መፍጨርጨር ነው ። ይሁን እንጂ በቤተ ልሔም ሲቀጣ አይፈልግም ፤ መቅረት ሳይሆን መዘግየቷ ራሱ ምን ሲደረግ !



Remove Watermark Now
pdfelement

# ምዕራፍ ዐሥራዐንድ

" … እረ መላ በሉ ወዳጅ ዘመዶቼ
ዐይን አፋር ሆኜ አለሁ ዐይን አፋር አይቼ

ሰላምታ አልሰጠኋት አላነጋገርኳት
በዐይን ብቻ እያየሁ ሦስት ወር ወደድኳት …. "

አቤል መተከዣያውን ሙዚቃ በለሆሳስ እያዜመ መኝታው ላይ ጋደም እንዳለ በዐይኑ ማፍቀር የጀመረበትን ጊዜ ርቀት ይለካ ጀመር ። ለሰዓት ያህል ዐይኑን መጽሐፍ ላይ ተክሏል ፤ ነገር ግን በፊደላት ፈንታ በርካታ የትዕግሥት ምስሎች ነበሩ - መጽሐፉ ውስጥ የሚነበቡለት ። ሳያስበው እርሳስ ከኪሱ አውጥቶ ስሌት ጀመረ ።

' ሦስት ወር ፣ ዐሥራ ሁለት ሳምንት ፣ ዘጠና ቀን ፣ ሁለት ሺህ አንድ መቶ ስድሳ ሰዓት ፣ አንድ መቶ ሃያ ዘጠኝ ሺህ ስድስት መቶ ደቂቃ ፤ ሰባት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሰባ ስድስት ሺህ ሴኮንዶች … . እንዴት በዚህ ሁሉ ጊዜ አንዲት ቃል እንኳ ሳልተነጋገራት እቆያለሁ ? እንዴት ይህን ያህል ጊዜ በዐይን ፍቅር ብቻ እንገላታለሁ ? ! አንድ ወንድ እንዴት ይህን ያህል ጊዜ ልቡን ለሴት ልጅ ይሰጣል ? ' እያለ ሲያሰላ ፣ ድንገት ሳምሶን ' ጉልቤው ' የመኝታ ክፍሉን በር ከፍቶ ዘው አለ ።

ከፀሐይ ላይ ስለ መጣ በስፖርት የዳበረው ጡንቻው ያብለጨልጭ ነበር ። አብዛኛውን ጊዜ በካኒቴራ ወይም በገርድ ሸሚዝ ነው የሚውለው ።

" ተነሥ ፣ ደብዳቢ መጥቶልሃል ። ስምህ ተለጥፎአል " አለው አቤልን ። አስገምጋሚ ድምፅ አለው ። ልማድ ሆኖበት ፣ ረጋ ብሎ መናገር አይችልም ። ባይቆጣም የተቆጣ ይመስላል ። አቤልን ይወደዋል ። አቤል ግን አጸፋውን አይ

Remove Watermark Now

# ምዕራፍ ዐሥራሁለት

እስክንድር ከነጋ ያጨሰውን ሲጋራ ብዛት ቆጠረ ። እኩል ቀን ከመሆኑ በፊት ዐሥራ አንድ አጭሷል ። ብር ልመና በገባበት ቢሮ ሲጋራ እየሰጡ ይሸኙታል ። ዊንስተን ከሚያጨሰው ዊንስተን ፣ ኒያላ ከሚያጨሰው ኒያላ ፣ ቤንሰን ከሚያጨሰው ቤንሰን ፣ ከባለርገምት ሮዝማን እየተቀበለ ሲያጨስ ይውላል ። ለወትሮው እስከ ምሳ ሰዓት ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ከሁለት ሲጋራ በላይ አያጨስም ነበር ። በዚህ ዕለት ግን በየጓደኞቹ ቢሮ ገብቶ የመጣበት ዓላማ ባልተሳካለት ቁጥር ፣ "ለማካካሻ" ሲጋራውን ሲለኩስ ቆጥሮ ዐሥራ አንድ አደረሰው ።

ትርፉ መቀጠል ነው ፤ ዕለቱ ከምሳው በኋላ በማጨስ ላይ ያለውን ዐሥራ ሁለተኛ ሲጋራ ግማሽ ወገቡ ላይ ቆርጦ ባለው ፓኬት ውስጥ ሌላ ሲጋራ አልነበረም ። ነገር ግን አድራሻቱ ከንቱ ቶሎ መሆኑን ልቡ ያውቀዋል ። ሲጋራ ለመተው በርካታ ጊዜ ሞክሯል ። በርካታ ጊዜ ምሏል ። በርካታ ጊዜ ኪሱ ውስጥ የቀሩ ሲጋራዎችን ሰብሯል ። መከራዎቹ ግም የሚያከናውነው እልክል ሲጠግብ ወይም በሌቶ ሲያርፍ ፣ ማለትም በከፍተኛ የጥሞት ጊዜያቶቹ ነው ። ነገር ግን ውሎ አድሮ ፣ እሳቱ ጋብ ሲልበት እምቢ ብሎ እጁን መሰብሰብ ያቅተዋል ። በዚህ በኩል ራሱን ገምቶ በቅቶታል ። ለሃያ ስድስት ዓመት ወጣት በስምንት ዓመት ያህል በሲጋራ ሳንባን ማታጠል ፣ ምን ያህል ሕይወት ላይ መቆለድ እንደሆን ይገባዋል ። ሰራሱም በጣም የሚገርመው ግን ፣ ብዙ ሲቸገር ለሲጋራ ማጨስ ወይም ሲጋራ ጋብኛ እለማማቱ ነው - ሱስ ምርኮኞቹ እንዳይከዱት ጸም ዴሎት እያደረጉ ወይም በእግልክት እያሰገደች የምትጠብቃቸው ይመስል ።

# ምስራቅ  በምዕራብነት

የማይሠው እውሩ መግለጫዎች ጽድ ሬቁ ብለዋል ። ወዲያ ወዲህ የሚያደርገውን ተማሪ እያታየዩም ። ሁሉም በየምኝት ዓይቱ ከመረቻቱ ጋር ፍልሚያ ይገለል ። እነዚያው በራሱ መሳይ የእንቅልፍ በዓቱን አሳጥርታል ። እንቅልፍ በሆይኑ ሳይሆን የሚያድርም እለ ። ውጥረቱና ግፊ ግቡ ሲታይ ፤ የተማሪትን ለመጀተን ሳይሆን ፤ የምትን ገዶል ለመግለል የሚያረጋግ ቅንነት ይመስለል ። ስለ ግል ጠንነትና ስለ እመ ጋገብ ፤ ጀገኑ የማያስርቡት ለዓምን ነው ። በየፉርሚያዎችው የጋራ ነገር ውስጥ ግዴለሽነት ነገም ይታያል ። ልብሶች ከገላ ሳይወለቁ ውስጠው ያድሬሉ ። የብዙ ተማሪ ጽጉር ከማበጠሪያ ተራርቆ ተቀብጣርቷል ። እናቆሽሹ በየእለለጋው ግርጌ የተ ጠራቀሙት የጫማ ሽራቦች እንጋሙተው ቢወረውሩእቸው ሰው ይፈነከታሉ ። [illegible] የሚገባው የሚያ [illegible] ክምር ፤ እንደገና [illegible] የፈተና [illegible] ማስብ ይረባል እንደ ተማሪውን የሚያርበተብትበት ለምን ፤

ዛይዮችና እርስ በእርስ መተማመን ጠፍቷል ። እንዱ ሌላውን ሊያምነውትው ሲጠጋ ፤ ከጥናት እንደ ማበርጋት ይቆጠራል ። "በኢል መስቀል" የሚሉት ፈሊጥ ተማሪው እርስ በእርሱ የሩሪጥ እንዲተገይ አድርጎታል ። የእንዱ ቀበሬ አብሮ የሚነሾው ባደኛው ሊሆን ይችላል ። መግረያ ባይማዘብት ከፍተኛ ሥርንት ነው ። ሽንት ቤት ይርሰው እስኪመለሱ የምትቃጠለኛ ጊዜ ታሳሳለች ። ማዕበሉ ማገን ጠርን ማገን እንደሚተው በውል ስለማይታወቅ ፤ ሁሉም ፈሉን ለማውጣት ይፍጨረጨራል ።

ከዚቶችና መኝታ ከፍሎች ውስጥ የጽቶ መማዝ ጠፍቷል ። መሲታወት ለማየት ወረፋ ቀርቷል ። ቅንድብ ለመከርከም

# ምዕራፍ ዐስራዘጠኝ

የጠዋት ፀሐይ ከመቼውም ይልቅ ፏ ብላ ወጥታለች ። "እኔንም እንዳንዴ አስታውሱኝ ፤ ስለእኔ ውበት ፤ ድምቀትና ሙቀት ተወያዩ" የምትል ትመስላለች ። ሆኖም ቀና ብሎ የሚያደንቃት ወይም ከልቡ ሆኖ የሚሞቃት ተማሪ አል ነበረም ። ሁሉም በየፊናው ይሯሯጣል ። ዛሬ የጠዋት እንቅልፍ የሚያሸንፈው ተማሪ የለም ።

ማዕበሉ በግቢው ውስጥ ተንሰራፍቷል ። ተማሪው ከንፈሩ ለመዳን ይተራመሳል ። ድምፅ የለሽ ትርምስ ይተራመሳል ። ወደ ፈተና ሲገቡ የሚያዝ ትጥቅን ለማሟላት ፤ እርሳስ ፤ ላጲስ ማስመሪያ ።

አንዳንዱ ሱሪው ገላው የከረመ ይመስል ሞግጓል ። ጸጉሩ ጸሎት እንደ ጎጆው ሁሉ ትንፋሽ አጥሮታል ። እንግዲህ በአንገት ሰላምታ እየተለዋወጡ መተላለፍ ብቻ ። የሁሉም ልብ የፍርሃት ደወል ይደውላል ። በጭንቀት ተወጥሮ ይንጥራል ።

የመፈተኛ አዳራሾቹ እንደ መቃብር አፋቸውን ከፍተው ይጠብቃሉ ። ቀድሞ የሚገባባቸው ተማሪ የለም ። ውስጡ ዙሪያውን ከብቦ የመጨረሻዎቹን ደወል ይጠባበቃል ። አንዳንዱ የሰዓቱንና የልቡን ትርታ ያዳምጣል ፤ እንዲህ የሚውጠው ትልቁ ደወል እስኪደውል ድረስ ! . . .

በመፈተኛው አዳራሾች አቅራቢያ የሚገኙት ሽንት ቤቶች በወረፋ ተጨናንቀዋል ። የገባው ቶሎ አይወጣም ። የሌለውን በግድ ያምጣል ። ከዚህ ምጥ በኋላ ትንሽ ጭርር እርጎ ይወጣል ። ከውጭ ያለው ያስጎመጉማል ። ያሳደባል ። ግን እሱም ሲገባ ያው ነው — የፈተና ምጥ !

# ምዕራፍ ሀያ

የከተማው ቀና ቀና መንገዶች በዩኒቨርስቲው ተማሪዎች መወረር ጀምረዋል ። የአራት ኪሎና አካባቢዋ ቡና ቤት አሳላፊዎች ፣ ለተማሪ ሻይ — ቡና በማቅረብ ተዋክበዋል ። የተማሪዎቹ እንሰሳዎች ፣ ልብሶችና በየሥርቻው ተወርውረው የከረሙ የእግር ሹራቦች ከመሃ በመታረቅ ላይ ናቸው ። ሐሜት ፣ ወሬና ፣ ዘፈንና ቀልድ ጊዜአቸውን ጠብቀው ተመልሰዋል ። በሲሚስተሩ ውስጥ በዩኒቨርስቲው የተደረጉት እንዳች ነገር ሳትቀር እየተነሱ መብጠልጠያ ጊዜ ነው ።

ይህ ሁሉ፣ ፈተና ማለቱን የሚያበሥር ነው ። የፈተናው ውጤት ቀርቦ ፣ ማዕበሉ ማንን መርጦ ፣ ማንን እንደ ተወ እስኪታወቅ ድረስ በሁለት ሳምንቱ የዕረፍት ቀናት አብዛኛው ተማሪ ከዚህ ክልል አይወጣም ።

አቢልና እስክንድርም የመጨረሻውን ፈተና እንደ ተፈተኑ ግቢውን ለቀው ወጥተዋል ። የተዝረከረኩ ዕቃዎችን ለማስተካከል እንኳ ፣ ወደ መኝታ ክፍላቸው አልተመለሱም ። ተያይዘው በቀጥታ ወደ እስክንድር እናት ቤት ተክለ ሃይማኖት አካባቢ ሔዱ ። አቢል ለዐውደ ዓመትና ሀአር በአርም ለዕረፍት እነ እስክንድር ቤት መሔድ የጀመረው ገና የሁለተኛ ዓመት ተማሪ ሳለ ከእስክንድር ጋር እንደ ተዋወቁ ነው ። እንዳንዴ አብረው ይሔዱና የተገኘውን ተማምረው ተመልሰው ይመለሳሉ ። ዘንድሮ ግን አቢል ቤታቸው ሳይሔድ ቆይቷል ።

“ የጠፋው ሰው ! እንደ ምን አላችሁ ፣ ልጆቹ ? ” አሉና እናትየዋ ፣ ሁለቱንም እቅፈው ሳሙዋቸው ።

“ አቢል ፣ ምነው እንዲህ ጠፋህ ልጄ ? ”

“ ምን እባክዎን ፣ ፈተና በዝቶ ነው ። ”

# ምዕራፍ ሀያአንድ

በማግሥቱ ጠዋት ከቀጠሮው ሰዓት ቀድሞ ያዲስ ባር የተገኘው እስክንድር ነበር ። ያደረበት ቤት ስላልተስማማው በሌሊት ነበር ተሾልኮ የወጣው ። የቤቱ አለ መስማማት ብቻ ሳይሆን ፣ የሰው ዐይን ፍራቻም ነው " አላሁ አክባር " ሳይል ያስወጣው ። የነዛ ኅሊናው ዐይን ሲያለቅስ እንባውን አድርቆ ሲልከሰከስ እያደረ ፣ የሌሎችን ዐይን ለምን እንደ ሚፈራ ሁሌም ይገርመዋል ። ባደረበት ቤት አንግቶ ፣ ተዝናንቶ ቆይቶ አያውቅም ።

‘ ይህን ልምድ ከየት ይሆን የቀዳነው ? ’ ሲል አሰበ ። በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በትምህርት ወራት ቀለም ላይ ተደፍቶ መክረም ፣ በዕረፍት ሰሞንታት ደግሞ ኪስ እስከ ተቻለ ድረስ በአልኮል ማበድና በየበረንዳው ማደር ልማድ እየሆነ መምጣቱ ነበር ያሳሰበው ። በዛሬው ዕለት እንዲ እንደ እሱው የሰው ዐይን እየፈሩ ፣ ካደሩበት በረንዳ በሌሊት እየተሾለኩ ፣ ጸጉራቸው እንደ ተንጨፈረረ ወደ ካምፓስ ሲሮጡ ያያቸው ተማሪዎች ቁጥር ትንሽ አልነበረም ።

‘ ሁኔታው በትምህርት ተጨንቆ የከረመን አዕምሮ የማዝናናት አዝማሚያ ይመስላል ’ ሲል ሐሳቡን ቀጠለ ። ‘ ታዲያ ከሰው ዐይንም ፣ ከነዛ ኅሊናም የማይሸሸበት ሌላ መዝናኛ መፍጠር አይቻልም ወይ ? ተማሪው ከተባበረ ፣ ከፈተና በኋላ ባለው የዕረፍት ጊዜ ውስጥ እንደየዓቅሙ ገንዘብ አዋጥቶ ፣ የሙዚቃና ሌሎች የተለያዩ ትርኢቶችን ፣ እንዲሁም አዝናኝና አነቃቂ ውድድሮችን ማዘጋጀት ፣ በቡድን ሆኖ ከከተማ ወጣ እያሉ ብርቅና ድንቅ ቦታዎችን መጐብኘትና የመሳሰሉት ልምዶች ቢዳብሩ ጤናማ መዝናኛ ይሆን ነበር ። ታዲያ ይህን በጐ ተግባር ለማስተባበር የግንባሩን ቦታ ማን ይውሰድ ? ’

# ምዕራፍ ሀያሁለት

ጊዜ ወደፊት አይገፈተርም ። ጊዜ ለሰው ጭንቀትም ሆነ ደስታ ደንታ የለውም ። የራሱን ሥርዓት ጠብቆ ነው የሚሄደው ፤ ያለፈ ጊዜ አይመለስም ፤ የወደፊቱ ደግሞ እንደ ፈለጉት ፈጥኖ አይመጣም ። ሰው በጊዜ ቁጥጥር ሥር ነው እንጂ ፣ ጊዜ በሰው ቁጥጥር ሥር አይደለም ። ሰዓት ሰው ሠራሽ ነገር ነው ፤ ምናልባት በማዞር ካለበት ሰዓት ወይም ደቂቃ ማስቀደም ይቻላል ። የቀን መቁጠሪያም ሰው ሠራሽ ነገር ነው ፤ አንዱን ወር ዐልፎ ሌላውን ወር ማየት ይቻላል ። ቀንን ገፍቶ ማስመሸት ወይም ምሽትን ገፍቶ ማንጋት ግን የማይቻል ነው ።

አቤል ቢቸግረው እንዲህ ዐይነት የጊዜ ምርምር ውስጥ ገባ ። ችግሩ ነው ምርምሩን የጋበዘው ። ቀኑ እስኪመሽለህ ፣ ሌሊቱ እስኪነጋልህ እያለው ተቸገረ ። በሌላው ተማሪ የዕረፍት ጊዜ ፣ ለእሱ ግን የመከራቸው ደስታ የሚያንቀት ጊዜ ሆኖበታል ። ቀንም ይቶዋል ፣ ማታም ይቶዋል ። ነገር ግን እንቅልፍ አይወስደውም ። እንዲሁ አልጋው ላይ እየተገላበጠ በሐሳብ መብከንከን ሆነ ። ጊዜ ከመቼውም ይልቅ የኋሊት እየተጎተተ የሚያቃስት መሰለው ።

ሳምሶን ለዕረፍቱ ወደ ቤቱ ስለ ሔደ መኝታ ክፍላቸው ውስጥ የቀሩት አቤል ፣ እስክንድርና " ድብርት " ብቻ ነበሩ ። " ድብርት " ፈተና ካለቀ በኋላ ፣ ያሳየው ለውጥ ቢኖር አልጋ ማንጠፉ ብቻ ነው ። በተረፈ እንደ ጥንቱ "ድብርት " ጥናቱም ቢቀር ያው አልጋውን በጋቢ ጋርዶ በራሱ ሕልም ውስጥ መኖሩን አልተወም ። ወደ ውጭም ቢወጣ ብቻውን ነው ።

እስክንድር የዕረፍት ጊዜ ጓደኛው መጽሐፍ ነው ። የአማርኛና የእንግሊዝኛ ልብወለድ መጽሐፎችን እየተዋሰ

# ምዕራፍ ሠላሳ

ማሰብና መጀመር የተለያዩ ሆነውበት ተቸግሯል — አቤል ። ሐሳቡ በጣም ይመጥቅበታል ። ሲጽፍ ያሰበው ነገር መጽሐፍ ይሆንበታል ። ሲሐስበው መጠም የሚያገኝ ሲትም አይመስለው ። ወረቀቱን ይዞ ቁጭ ሲል ግን፣ ከብዕሩ ጠብ የሚል ነገር ይጠፋል ። ባዶ ወረቀት ላይ ፣ "ማን ፎር ሂምሰልፍ" ከሚል አርዕስት ጋር መፋጠጥ ብቻ !

'ችግሩ ከቋንቋው ይሆን ?' ሲል አሰበ ። 'በሰው ቋንቋ ከምቸገር ሐሳቤን እንደ ልቤ ለንቆረቁርበት በምችለው በራሴ ቋንቋ ለምን አልጽፍም ?'

ባዶውን ወረቀት ከአጠገቡ አገለለና መጽሐፍ ገለጠ ። ለጽሑፉ የሚጠቅሙትን መጽሐፎች መርጦ ከሥሩ ጠረጴዛው ላይ ከምሯል ። መጻፍ ከመጀመሩ በፊት ግን ከ ዕለቱ ጉዳይ ላይ የጻፉ ብዙ መጽሐፎችን ማንበብ እንዳለበት ስለ ተረዳ በየምንን እያነበበ ነበር ። ችግሩ ግን ከያዘው መጽሐፍ ላይ ብዙ ሰዓት መቆየት አለ መቻሉ ነው ። ከመጽሐፉ ውስጥ ጠቃሚ ሐሳብ ሲያገኝ የእሱ ሐሳብ ቀድሞ ይመጣበትና ጻፍ ጻፍ ይለዋል ።

አሁንም ከተቀመጠበት ተነሥቶ ትንሽ ተንጎራደደ ። ከመንጎራደዱ ጋርም የሚጽፈው ነገር ብልጭ አለለት ።

ሰው ከራሱ ጋር የሚጣላው ለምንድነው ? በግል ምኞትና ግብ እአምሮው ተወጥሮ ሲጨነቅ ነው ። ነገር ግን የሰው ልጅ የመጨረሻ ግቡ እኛ እንጂ፣ እኔ መሆን የለበትም ። ከራሱ ጋር ሊታረቅ የሚችለው በዚህ እምነት ተጠምቆ ከግሉ ይልቅ ለማኅበራዊ ችግር ክብደት ሲሰጥና ደስታውን ከኅብረተሰቡ ጣፋጭ ሕይወት ውስጥ ለማግኘት ሲሞክር ነው ። ሰው በመጀመሪያ ለሕያውነቱ ከፍተኛ ግምት

ትዕግሥት ከአቤል ዐይን ዳርቻ ላይ ዐይን እር አየች ። ሊትጠርግለት ብትሞክርም እጅዋ ይንቀጠቀጥ ይሆን ... ምንም ደፍራ እጅዋን ዘርግታ በጣቷ አነሣችለት ።

" ምንድን ነው ? " አላት ከንፈሩ እየተንቀጠቀጠ ።
"ጉድፍ " አለችው ፤ የእሷም ከንፈር እየተንቀጠቀጠ ።

ዐይኑን የነካው እጅዋን ጥብቅ አድርጎ ሳመው ።

የናታንና እስክንድር በደስታ ፈዘው ቀሩ ። እውን ሳይ ሆን የፊልም ትርኢት የሚያዩ ነበር የመሰላቸው ። በተለይ እስክንድር ራሱን መቆጣጠር አቅቶት፣ እንዴ ሕፃን ፈንደቅ ፈንደቅ የሚል ስሜት ታገለው። ደስታ በጣቅ ፣ ጣቅም በጥርስ የሚገለጽ ነገር ባይሆን ኖሮ መላ ሰውነቱ እየጣቀ ነበር ።

ለአፍታ ያህል ዓይኖቻቸው ፊቱ ላይ ድቅን አሉበት ። ማርታ የነገር ቅንድቧን እያርገበገበች ፣ ድብርት በጋቢው ተጀቡና እየተልጉመጉመ ፣ ሚስተር ሆርስ ቼሱን ታቅፎ ቅሬታውን እንደ ዘራ ፣ ቤተልሔም በሬተና ... ወደ ሽንት ቤት እየሮጠች ፣ ሳምሶን ጥሊቤው ... ጥር ለአቤል ሲማታለት እየተጋዘ — ሁሉም በእስክንድር ሐሳብ ውስጥ ተሰለፈ ። 'ምነው እነዚህ መጥተው ይህን ትርኢት ለማየት በታደሉ ! ' አለ በልቡ ።

አቤል የትዕግሥትን እጅ ስሞ አልለቀቀውም ። እን ደገና ወደ ደረቱ አስጠግቶ ጥብቅ አርጐ ያዘው ። እጅዋ እንደ ኤሌትሪክ ኸብ የአቤልን ልብ ትርታ እየተቀበለ ወደ እሷ ያስተላልፍ ጀመር ። ትርታው ነዘረት አንፈገፈገ ችም ። ይልቁንም መላ ሰውነቷን በዝግታ ወደ አቤል እካል አስጠጋችው ። ትንፋሻቸው ተገጣጠመ ። ሁለቱ እንደ አንድ ሰው !

" እ — እ — እወድሻለሁ ። "
አስቸጋሪው የኖረችውን እንጊት ቃል ተነፈሳት ።